Gaafa: 01/07/2017
Date: تاريخ

Lakk.:07/stm/abo/2017
No.: رقم

## የኦሮሞ ህዝብ ስልቱን ቀይሮ ለመተግበር የታቀደውን የፊንፊኔ ማስተር ፕላን እቅድ ፈጽሞ ኣይቀበልም!

*የኦሮሞ ነጻነት ግንባር መግለጫ*

የወያኔ መንግስት ሰሞኑን በሚኒስትሮች ካቢኔው ኣማካይነት ኦሮሚያ ከፊንፊኔ ማግኘት የሚገባትን ልዩ ጥቅም በተመለከተ ረቂቅ ኣዋጅ ኣውጥቷል። በፋሽስታዊ ስርዓቱ መግለጫ መሰረት ረቂቅ ኣዋጁ እንዲጸድቅ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይቀርባል። የኦሮሞ ህዝብና የነጻነት ትግሉ መሪ ድርጅት፡ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ይህንን ኣዋጅ ፈጽሞ ኣይቀበሉም።

በዲሞክራሲ ሽፋንና በጠመንጃ ኣፈሙዝ ኢትዮጵያን እየገዛ ያለው የኣናሳ ቡድን ስርዓት የኦሮሞን ህዝብ በመወከል ውሳኔ ለመስጠት ህጋዊ መብት ስለሌለው እንዲጸድቅ ለስርዓቱ ፓርላማ የቀረበው ረቂቅ ህግ ተቀባይነት ኣይኖረውም። ፊንፊኔ ከኣንድ ምዕተ-ዓመት በፊት በጠላት ተወርራ የተያዘች የኦሮሞ ህዝብ መኖሪያ ናት። የኦሮሞ ህዝብም በተፈጥሮ የተቸረውን መሬቱን ለማስመለስ ሲታገል ዛሬን ደርሷል። የንብረት ኣጠቃቀም ስርዓትንም ሆነ ከፊንፊኔ ከተማ ነዋሪዎች የኑሮ ሁኔታ ጋር ትስስር ያለው ውሳኔ ሊተላለፍ የሚችለው በህጋዊ የኦሮሞ ህዝብ ወኪሎች ብቻ መሆን ይገባዋል። የኦሮሞ ህዝብ የኢትዮጵያን ኢምፓዬር እያስተዳደረ ባለው ኣናሳ ኣምባገነናዊ ስርዓት ስር ይህን መሰል ወኪል የለውም። የትግራይ ህዝብ ነጻ ኣውጪ ግንባር(ሕወሃት) ሆነ ቅጥረኛ ተላላኪው ኦፒዲኦ በኦሮሞ ህዝብ ስላልተመረጡ ህዝቡን በመወከል እንዲህ ባለው ወሳኝ ጉዳይ ላይ ውሳኔ የመስጠት መብት የላቸውም።

የሕወሃት/ኢህኣዴግ ቡድን በ2015ዓም ውስጥ የተካሄደውን የይስሙላ ምርጫ በመስረቅ 100% ማሸነፉን ማወጁ ይታወሳል። የሃሰት ምርጫው ድራማ ከተከወነ ከጥቂት ወራት በኋላ የኦሮሞ ህዝብና በኢትዮጵያ ውስጥ በሌሎችም ክልሎች የሚገኙ ብዙሃን ህዝቦች ወደ ጎዳና ወጥተው ሰልፍ በማካሄድ ለጨቋኙ መንግስት ያላቸውን የኣንገዛም-ባይነት ተቃውሞ በኣደባባይ ኣሳይተዋል። ይህ መንግስት ነኝ ባይ ቡድን ይህን የህዝቦች ቅሬታና ተቃውሞ ኣድምጦ ምላሽ ለመስጠት ከመስራት ይልቅ እንደልማዱ ህጻናትና ተማሪዎች፥ ሴቶችና ኣዛውንትን እጅግ ዘግናኝ በሆነ ሁኔታ በመግደል የህዝቦችን ጥያቄ ለማፈን በመሞከር ላይ ኣተኮረ። በዚህም ከ2000 የሚበልጡ የኦሮሞ ዜጎች በጠራራ ጸሃይ ተገደሉ፥ በኣስር ሺዎች የሚቆጠሩ ደግሞ በስርዓቱ ሃይሎች መታሰር፡ መደፈር፡ ለሰቆቃ መዳረግና ታፍነው መሰወር እጣ ፈንታቸው ሆነ።

ጥቅምት 2 ቀን 2016ዓም ብቻ ከ700 በላይ የሚሆኑ ዜጎች ቢሾፍቱ ሀርሰዴ ላይ በተከበረው ታላቁ የኦሮሞ የምስጋና በዓል፡ ኢሬቻ ላይ ወያኔ ባሰማራቸው ሃይሎች ህይወታቸው ተቀጠፈ። ለተፈጸመው ለዚህ ዘግናኝ ወንጀል ለህግ ተጠያቂነት የቀረበ ኣንድም ሰው የለም።

የሕወሃት ቡድን ህዝቡ የጭካኔ ግድያና ዘግናኝ ወንጀል በከፍተኛ ደረጃ ቢፈጸምበትም ተፈጥሮኣዊና ህገ-መንግስታዊ መብቶቹን ለማስከበር በቆራጥነት ትግሉን ለመቀጠል መወሰኑን በመገንዘብ፡ የኣስቸኳይ ጊዜ ኣዋጅ ኣውጆ የበለጠ ኣፈና መፈጸምን እንደመፍትሄ ወሰደ። በኣሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝቦች የስርዓቱ የጦርና የደህንነት ሃይሎች ዜጎችን ያለህጋዊ ኣግባብ እንዲገድሉ፥ እንዲያሰቃዩና እንዲያዋክቡ መብት በሰጣቸው ኣዋጅ በየቀኑ በታጠቁ ሃይሎች እየተገደሉና ወህኒ እየተወረወሩ ለሰቆቃ በመዳረግ ላይ ናቸው። እንዲህ በመሰለው ሁኔታ ውስጥ ኦሮሚያ ከፊንፊኔ ማግኘት የሚገባት የተባለውን ልዩ ጥቅም ያለህዝብ ፍላጎትና ውይይት ኣርቅቆ ማቅረብ በሌላ በኩል ደግሞ ባለጉዳዩን ህዝብ የሰብዓዊ መብቶቹን ነፍጎ ማሰቃየት ከዘር ፍጅት የሚስተካከል ተግባር ነው።

ለሕወሃት ስርዓት ፍጻሜ ማበጀትን ዓላማው ያደረገው ብሄራዊ ንቅናቄ ስልቱን ቀይሮ እየተፋፋመ ባለበት በዚህ ወቅት ወያኔ ሰላም የሰፈነ አስመስሎ በመደስኮርና የይስሙላ ለውጥ በመደርደር ህዝቦችንና ኣለምኣቀፍ ለጋሾቹን ለማታለል እየሞከረ ነው። ከተደረጉት የይስሙላ ለውጦች መካከል ኣንዱ በስርዓቱ ካቢኔ ውስጥ የኦሮሞ ህዝብ ውክልና ከፍ ብሎ የታየ ለማስመሰል የሚኒስትሮች ካቢኔ የተባሉ ተላላኪዎቹን መቀያየሩ ነው። እየተፋፋመ ያለውን የኦሮሞ ህዝብ ብሄራዊ የጭቆና ፍጻሜ ንቅናቄ ለማፈን በማቀድ ስርዓቱ በኦሮሞ ህዝብ ስም የሾማቸውን ሚኒስትሮች ቀረብ ብለን ካየናቸው ኣብዛኛዎቹ በተለይም በመንግስት ቁልፍ የሃላፊነት ቦታዎች የተሰጣቸው ከኦሮሞ ኣብራክ ያልወጡ ግን ኣፋን ኦሮሞ መናገር የሚችሉ ኣልያም ደግሞ በህይወት ዘመናቸው ሙሉ ኦሮሞነታቸው ሲክዱ የኖሩ መሆናቸውን መረዳት ኣያዳግትም። የወያኔ መንግስት እነዚህን የመሳሰሉ ሚኒስትሮችና መሰል ተላላኪ የካቢኔ ኣባላትን ይዞ ነው የረቂቅ ህጉን ለ"ሚኒስትሮች ካቢኔ" ተብዬ ኣቅርቦ ለማስጸደቅ እያሴረ ያለው።

ይህ ረቂቅ ተብዬው ህግ ላይ ላዩ የኦሮሞ ህዝብ ከፊንፊኔ ማግኘት የሚገባውን ጥቅም ለማስጠበቅ የተደረገ ለውጥ መስሎ ይቅረብ እንጂ ያለው እውነታ ረቂቅ ኣዋጁ ተቀባይነት ያጣውን የፊንፊኔ ማስተር ፕላን መልሶ በስራ ላይ ለማዋል በማቀድ የተወጠነ ሴራ ነው። ይህንን በይበልጥ ግልጽ የሚያደርገው ረቂቅ ህጉ በኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ በፈጸሙት ዘረፋ በኣጭር ጊዜ ውስጥ ቢሊየነሮች የሆኑት የሕወሃት መሪዎችና ጀሌዎቻቸው መሬታችሁ ለልማት ይፈለጋል በሚል የኦሮሞ ዜጎችን ከኣያት ቅድመ-ኣያቶቻቸው መሬት ላይ ከማፈናቀል የሚገታቸው ምንም የቁጥጥር ስርዓት ኣለማካተቱ ነው። ይህንን የዘረፋ ስልት ይበልጥ ለመተግበር ለመሬቱ ባለቤቶች "መሬቱ ከሚያወጣው ዋጋ ጥቂት ኣብላጫ" ካሳ ከፍሎ በማፈናቀል ፍላጎታቸውን ማሟላት ነው። የዚህ ፕሮጀክት ኣተገባበርም የሚወሰነው በሕወሃት ሹማምንት ኣልያም በቅጥረኛ ተላላኪዎቹ ይሆናል። የመሬቱ ባለቤቶች የተጠቀሰውን ካሳ ወስደን ከመሬታችን ኣንፈናቀልም ካሉ የፍትህ ስርዓቱ ሙሉ በሙሉ በወያኔ ቁጥጥር ስር በመሆኑ ኣቤት ብለው ፍትህ የሚያገኙበት ቦታ የለም። የሚገርመው ይህ ረቂቅ ኣዋጅ ቤተሰቦችን ከቀዬኣቸው የማፈናቀሉ ተግባር በህዝቡ ቋንቋ፡ ባህልና ማህበራዊ የኑሮ ሁኔታ ላይ ያለውን ጫና በተመለከተ የጠቀሰው ኣንድም ነገር ኣለመኖሩ ነው።
ይህ ህግ የሚያበረታታው በገደብ-የለሽ የከተሞች መስፋፋት የኦሮሞን ህዝብ ታሪካዊ የኣሰፋፈር ሁኔታ ማጥፋት ብቻ ሳይሆን የኦሮሞን ታሪካዊ ቦታዎች፡ ባህልና ወጉን የሚያንጸባርቁ፡ ባጠቃላይ የኦሮሞ ህዝብ ሃብትና ማንነቱን የሚያንጸባርቁ እሴቶችን ማውደም ነው። ይህም የዘር ማጥፋት ወንጀል በመሆኑ ሁሉም ሊጋፈጠው ይገባል።

የወያኔ መንግስት በረቂቅ ኣዋጁ ውስጥ የኣካባቢውን ህዝብ ለኣደጋ የሚያጋልጠውን ብክለት ለመቆጣጠር የሃሰት ቃል ቢገባም የፊንፊኔ ከተማ ለራሷ የፍሳሽና የቆሻሻ ማስወገጃና መቆጣጠሪያ ስርዓት እንዲሁም መሬትን በቀጠይነት መጠቀም የሚያስችል ኣንዳችም የቁጥጥርና የኣስተዳደር ስርዓት የላትም። እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ጥያቄ ይህ በሆነበት ሁኔታ ውስጥ የከተሞች ማስፋፊያ እቅዱ በምን መልኩ ነው በፊንፊኔ ዙሪያ ነዋሪው ማህበረሰብ ላይ ጉዳት የማያስከትለው? የሚለው ነው።

በረቂቅ ህጉ የተጠቀሰው ሌላው ፌዝ በፊንፊኔ ከተማ ውስጥ ኣፋን ኦሮሞን መማርና በቋንቋው መጠቀምን የተመለከተ ነው። በህጉ መሰረት ልጆቻቸው በኣፋን ኦሮሞ እንዲማሩ "ለሚፈልጉ" የኦሮሞ ኣርሶኣደሮችና የከተማ ነዋሪዎች የፊንፊኔ ከተማ ኣስተዳደር የኣንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሊከፍትላቸው ይገባል የሚል ነው። ኣፋን ኦሮሞ ኣርሶኣደሮች ቋንቋና የከተማ ነዋሪዎች የማይፈልጉት ቋንቋ ተደርጎ መገለጹ ከመሃይምነትና ድንቁርና የመነጨ ከፍተኛ ንቀትና ታሪክ ይቅር የማይለው ወንጀል ነው። ለህንድ፡ ለግሪክ፡ ለኣርሜንያና ለሌሎችም ዜጎች ትምህርት ቤት ተፈቅዶ ትምህር እየተካሄደ ባለበት በዚህ ወቅት በረቂቅ ህጉ ውስጥ የተቀመጠው ውሳኔ፡ ኣፋን ኦሮሞ በሃገሪቷ ውስጥ ለመናገርም ሆነ በቋንቋው ለመማር ላለፉት መቶ ሃምሳ ዓመታት ሲከለከል የነበረ ቋንቋ ለመሆኑ ማስረጃ ነው። ከዚህም ሌላ የወያኔ ስርዓት በፊንፊኔ ውስጥ የሚኖሩ የኦሮሞ ዜጎች በቋንቋቸው የመማርን መሰረታዊ መብት በመንፈግ በኣንደኛ ደረጃ ትምህርት ብቻ መገደቡ የኦሮሞን ማንነት ለማጥፋት በስልት እየተካሄደ ያለ ዘመቻ ኣካል መሆኑን ይመሰክራል። ሰሞኑን የተደረገው የቁቤ ኣፋን ኦሮሞ ፊደላት ተርታ ለውጥም የኦሮሞን ቋንቋ፡ ባህልና ማንነት የማጥፋት ዘምቻ ኣካል ነው።

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ይህ ረቂቅ ኣዋጅ የወንጀለኞችና የሽፍቶች ቡድን የኦሮሞን መሬት በመዝረፍና ኦሮሚያን በመሸንሸን የፊንፊኔን ማስተር ፕላን መልሶ ስራ ላይ ለማዋል የመሞከር፡ በዚህም የኦሮሞን ብሄርተኝነት ለማዳከር ያለመ ኣዲስ ሴራ ኣካል መሆኑን ለኦሮሞን ህዝብ ያስገነዝባል።

**ሰፊው የኦሮሞ ህዝብ ሆይ!**

ልጆችህን፡ ነፍሰ-ጡር ሴቶችንና ኣዛውንቶችን በጭካኔ የገደለ ኣምባገነን ቡድን የሚጠቅምህን ህግ ሊያረቅልህ ኣይችልም። ይህ የሽፍቶች ቡድን በጠመንጃ ኣፈሙዝ ወደ ስልጣን ወጥቶ ንብረትህን በመዝረፍና በማውደም ከኣለም ከበርቴዎች ተርታ ተሰልፏል። በስልጣን ላይ በሰነበተባቸው ዓመታትም የዘር-ማጥፋትና የከፋፍሎ መግዛትን ስልት ባንተ ላይ በመተግበር በብዙሃንነትህ ያለህን ሃይል ለማዳከም ደባ ሲፈጽምና ሲንቀሳቀስ ዛሬን ደርሷል። በኣሁኑ ወቅት ስልጣን ላይ ያሉት የሕወሃት መሪዎችም በመተግበር ላይ ያሉት የቀድሞው የስርዓቱ ቁንጮ፡ መለስ ዜናዊ "ብዙሃንን ህዝብ ወደ ኣናሳነት መለወጥ ይቻላል " የሚለውን የጠላትነት እቅድ ነው።

**ለሙብትህ መከበር በትግል ላይ ያለኸው ህዝባችን ሆይ!**

ለረዥም ዓመታት ባንተና በማንነትህ ላይ ያነጣጠረውን ዘመቻ ስትቀለብስ ዛሬን ደርሰሃል። በተለይ ደግሞ ባለፉት ሁለት ዓመታት ለ25 ዓመታት ሲገነባ የነበረውን የኣምባገነኑን ስርዓት የደህንነትና የስለላ መዋቅር በጣጥሰህ የስርዓቱን ክፋትና ሴራ እንዲሁም ዘግናኝ ወንጀሎች ለኣለም ኣጋልጠሃል። ይህን ኣንተን በማውደም ስልጣን ላይ ለመሰንበት የሚያልመውን ኣምባገነን ስርዓት ገፍተህ ከመቀበሪያው ጉድጓድ ኣፋፍ በማድረስህ የቀረው ኣማራጭ ገደል ገብቶ መጥፋት ኣልያም እጅ መስጠት ብቻ ሆኗል። የሚታየው እውነታ ይህ ሆኖ ሳለ፡ ይህ ኣምባገነን ስርዓት ግን የፈጠረውን ችግር ከመፍታት ይልቅ በኣስቸኳይ ጊዜ ኣዋጅ ስርዓቱን ለመታደግ መሯሯጥን ሆኗል። ለዚህ ኣምባገነን ቡድን ፍጻሜ ለማበጀት ጀግኖች ልጆችህ፡ ቄሮና የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በኣዲስ ስልት መንቀሳቀስ ነው ለነጻነታችን የመጨረሻው መፍትሄ የሚሆነው።

ስለሆነም ስርዓቱን በማገልገል ላይ ያሉ የኦሮሞ ተወላጆችን ጨምሮ በሃገር ቤትና በውጪ ሃገራት ያለው ህዝባችን የወያኔ ስርዓትን እውነተኛ ማንነት በሚገባ በመገንዘብ ለጭቆና ፍጻሜ ማበጀትን ያለመ የመጨረሻ ንቅናቄ ለማካሄድ እራሱን እንዲያዘጋጅ ኦነግ ጥሪውን ያቀርባል። ከፊታችን ያለው ጉዞ ፈታኝ ቢሆንም ድሉ የኛ እንደሚሆን ጥርጥር የለንም። ኣሁን ያለንበት ወቅት የህብረት ክንዳችንን ይበልጥ የምናጠናክርበትና በኣስፈላጊው መንገድ ሁሉ ጨቋኙን ስርዓት ከህዝባችን ጫንቃ ላይ ለማሽቀንጠር ከነጻነት ታጋዮች ጎን መሰለፍን የሚጠይቅ ወሳኝ ጊዜ ነው።

በመጨረሻም የኣለም ማህበረሰብ ይህን በኢትዮጵያ ውስጥ እየተፈጸመ ያለውን ሁኔታ በሚገባ እንዲከታተልና እንዲመዘግብ እየጠየቅን፡ በኢምፓዬሪቷ ውስጥ ያለው ችግር ወደ ባሰ ኣስከፊ ደረጃ ሳይሸጋገርና ጊዜው ሳያልፍ ሃገሪቷን እየገዛ ባለው ቡድን ላይ ጫና እንዲያሳድር እንጠይቃለን። ስልጣኑን በተቆጣጠረው ቡድን በኣይናችሁ ፊት እጅግ ዘግናኝና ኣረመኔያዊ ወንጀል እየተፈጸመ ባለበት በኣሁኑ ወቅት፡ እንዳላያችሁና እንዳልሰማችሁ ዝምታን መምረጣችሁ ኣሳፋሪ ነው። የኣለም ማህበረሰብ የሕወሃት ስርዓት እያደረሰ ያለውን ኣደጋ የሚከላከል እርምጃ በኣስቸኳይ የማይወስድ ከሆነ በኣጠቃላይ የኣፍሪካ ቀንድ ቀጣና ሰላምና መረጋጋት ለከፋ ኣደጋ እንደሚጋለጥ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ያስገነዝባል። ኣስተዳድራቸዋለሁ የሚላቸውን ህዝቦች የሚያሸብር ስርዓት የጸረ-ሽብር ዘመቻ ኣጋር ሊሆን ኣይችልም።

**ድል ለኦሮሞ ህዝብ!**

**የኦሮሞ ነጻነት ግንባር**

**ሓምሌ 1, 2017ዓም**